ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ
አውቃፍ ሚኒስትር

ጁማዳል አወል ፰/፲፬፵፩ ሂ.
ጃንዮሪ ፫/፳፻፳ ግ.

# ከአላህ (ዐ.ወ.) ጋር ወደመሆን የመግባት ምክኒያትና መልካም ውጤቱ

ምስጋና ሁል በተከበረው መጽሐፉ

{هُوَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ اسْتَوَى عَلَى الْعَرْشِ يَعْلَمُ مَا يَلِجُ فِي الْأَرْضِ وَمَا يَخْرُجُ مِنْهَا وَمَا يَنْزِلُ مِنَ السَّمَاءِ وَمَا يَعْرُجُ فِيهَا وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنْتُمْ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}

ለአላውለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው ትርጉሙም (
ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፡፡ ከዚያም (ለክብሩ በሚስማማ መልኩ) በዐርሹ ላይ ተደላደለ፡፡ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና አስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

ከአላህ (ዐ.ወ.) ጋር መሆን ማለት አላህ የሚቆጣጠረው እንድሁም አላህ የሚያግዘው መሆንን ማወቅና በልብ ማዘውተር ማለት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የፍጥረታቱን ሁሉ እንቅስቃሴ በእወቀቱ የሸፈነ መሆኑን እንድህ በመለት ጠቁሟል

{وَعِندَهُ مَفَاتِحُ الْغَيْبِ لَا يَعْلَمُهَا إِلَّا هُوَ وَيَعْلَمُ مَافِي الْبَرِّوَالْبَحْرِومَاتَسْقُطُ مِن وَرَقَةٍإ لَّايَعْلَمُهَا وَلَاحَبَّةٍ فِي ظُلُمَاتِ الْأَرْضِ وَلَارَطْبٍ وَلَايَابِسٍ الا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ}

ትርጉሙም (የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፡ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም፡፡ በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል፡፡ ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ፡፡ ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**( أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجۡوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمۡ وَلَا خَمۡسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمۡ وَلَآ أَدۡنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكۡثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمۡ أَيۡنَ مَا كَانُواْۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُواْ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ)**

ትርጉሙም (አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መኾኑን አታይምን? ከሦስት ሰዎች መሾካሾክ አይኖርም እርሱ አራተኛቸው ቢኾን እንጅ፡፡ ከአምስትም (አይኖርም) እርሱ ስድስተኛቸው ቢኾን አብሯቸው ቢሆን እንጅ፡፡ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) እርሱ የትም ቢኾኑ እንጂ፡፡ ከዚያም በትንሣኤ ቀን የሠሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) ፍጡሩን ሁሉ ያግዛል፣ ስኬትን ይለግሳል፣ ይጠብቃል፣ ይጠግናል እንድሁም ይንከባከባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ከባሮቹ ነብያቱን ወልዮቹንና ፃዲቃንን ከነሱ ጋር በመሆን ከሌሎች ባሮቹ ለይቷቸዋል፡፡ ይህን ከፍጥረታቱ የመረጣቸው ባሮቹ የተቸሩትን ታላቅ አብሮነት ቅዱስ ቁርኣን በበርካታ ምእራፎች የጠቀሰው ሲሆን አላህ (ዐ.ወ.) በሰይዲና ሙሳና በሰይዲና ሃሩን ልሳን እንድህ ሲል የጠቀሰው በቅድሚያ ይወሳል፡

**{اذْهَبْ أَنْتَ وَأَخُوكَ بِآيَاتِي وَلَا تَنِيَا فِي ذِكْرِي * اذْهَبَا إِلَى فِرْعَوْنَ إِنَّهُ طَغَى * فَقُولَا لَهُ قَوْلًا لَيِّنًا لَعَلَّهُ يَتَذَكَّرُ أَوْ يَخْشَى * قَالَا رَبَّنَا إِنَّنَا نَخَافُ أَنْ يَفْرُطَ عَلَيْنَا أَوْ أَنْ يَطْغَى * قَالَ لَا تَخَافَا إِنَّنِي مَعَكُمَا أَسْمَعُ وَأَرَى}**

ትርጉሙም («አንተም ወንድምህም በተዓምራቶቼ ኺዱ፡፡ እኔንም ከማውሳት አትቦዝኑ፡፡ «ወደ ፈርዖን ኺዱ፡፡ እርሱ ወሰን አልፏልና፡፡ «እርሱም ይገሰጽ ወይም ይፈራ ዘንድ፤ ለእርሱ ልዝብን ቃል ተናገሩት፡፡» «ጌታችን ሆይ! እኛ በእኛ ላይ ክፋት በመሥራት መቸኮሉን ወይም ኩራትን መጨመሩን እንፈራለን» አሉ፡፡ (አላህም) አለ «አትፍሩ፡፡ እኔ በእርግጥ ከእናንተ ጋር ነኝና፡፡ እሰማለሁ፤ አያለሁም፡፡) ማለት ነው፡፡

ይህን አብሮነት የነብዩ ሙሳ ህዝቦች ‹እኛ ፈርዓውንና ወታደሮቹ የሚደርሱብን ነን› ባሉ ጌዜ ነብዩ ሙሳ ተ‹ዉ ጌታዬ ከኔ ጋር ነው በእርግጥ ይመራኛል› በማለት የፈጣሪ ረድኤትና ድሉ የማይለያቸው መሆኑን በእርግጠነት እንዲናገሩ ያደረጋቸው ነው፡፡

የዚህ አይነት የአላህ እርዳታ አብሮነት ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከባልደረባቸው ከአቡበክር አሲዲቅ ጋር ስደት በወጡ ጊዜ በግልጽ የታዬ ሲሆን (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አቡ በክር አሲዲቅ እንድህሲሉ አብራርተውታል፡ (እኔ ከነብያችን ጋር በዋሻው በነበርኩበት ወቅት ወደአጋሪዎች ጫማዎች ተመለከትኩና ‹የአላህ መልክተኛ ሆይ! አንዳቸው ወደጫማው ቢመለከት ቀጥታ ያየናል አልኩኝ፡፡› ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (አቡ በክር ሆይ! (አላህ ሦስተኛቸው በሆኑ ሁለት ሰዎች ምን ትገምታለህ) አሉኝ፡፡ ይህን ጉዳይ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል ገልጾታል፡

**{إِلَّا تَنْصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُوا ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لَا تَحْزَنْ إِنَّ اللَّهَ مَعَنَا فَأَنْزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُوا السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ} .**

ትርጉሙም ((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል ለእርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

አንድ ባሪያ ምንጊዜም አላህ ከሱ ጋር መሆኑን አለመዘንጋቱ ታላቅ ነገር ነው፡፡ አላህ ከሱ ጋር የሆነ ሰው ደጋፊውም ይሁን ተቀናቃኙ ምንም አያሳስበው፡፡ አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር እንዲሆን ካሰበ ወደሱ በሚያደርሰው ቀጥተኛ መስመር መጓዝ አለበት፡፡ እንድሁም ለሱ መሰረትየ ሆኑ ነገሮችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ በመጀመሪያ ትክክለኛ ሙእሚን መሆን አላበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አላህ በእርግጥ ከመእምናን ጋር ነው ይላል፡፡ አንድ ሰው ምእምን ይባል ዘንድ በአላህ፣ በመላእከት፣ በመጽሐፍት፣ በመልክተኞችና በመጨረሻው ቀን እንድሁም በጎም ይሁን መጥፎ ነገሮች በሙሉ ከአላህ ዘንድ የተፈረዱ በመሆኑ ማመን አለበት ስንል የዚህ እምነቱ ገጽታ በአለው ስነ ስርኣትና ከሰዎች ጋር በሚዋዋልበት ወቅት ጎልቶ መታየት አለበት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና ከእጁ ተንኮል የዳኑ ነው፡፡ ሙእሚን ማለት ደግሞ ሰዎች በሕይዎታቸውና በገንዘባቸው እመነት የጣሉበት ነው፡፡)

አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር ይሆን ዘንድም አላህን ፈሪና በጎ ሰሪም መሆን አለበት፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) አላህ ከነዚያ እሱን ከሚፈሩትና ከመልካም ሰሪዎች ጋር ነው ይላል፡፡ እንድሁም እወቁ አላህ ከነዚያ እሱን ከሚፈሩት ጋር ነው ይላል፡፡ አሁንም አላህ ከነዚያ መልካም ከሚሰሩት ጋር ነው ይላል፡፡ አላህን መፍራት ማለት አላህ

የሚወደውን ነገር መሥራት እሱን ከሚያስቆጣ ነገር ሁሉም መራቅ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መልካም ነገርን ሁሉ ኣካቶ ይዟል፡፡ ቅዱስ ቁርኣን ኣላህን መፍራት ምን ማለት እንደሆኑ እነደሚከተለው ጠቁሟል፡፡

**{لَيْسَ الْبِرَّ أَن تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّـهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِوَالْمَلَائِكَةِوَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ وَأَقَامَ الصَّلَاةَ وَآتَى الزَّكَاةَ وَالْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَاعَاهَدُواوَالصَّابِرِينَ فِي الْبَأْسَاءِ وَالضَّرَّاءِ وَحِينَ الْبَأْسِ أُولَئِكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُتَّقُونَ} .**

ትርጉሙም (መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሶላትንም ደንቡን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ፣ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፡፡ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ታጋሾችን (እናወድሳለን)፡፡ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው፡፡ እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ አንዳችሁ ሌላውን አይመቅኝ፣ እንድሁም አንዳችሁ በሌላችሁ ላይ አይጫረት፣ አትጠላሉም፣ ጀርባም አትሰጣጡ፡፡ አንዳችሁም የሌላውን ነውር አያውጣ፣ ወንድም ተማማች የአላህ ባሪያዎች ሁኑ፡፡ ሙስሊም የሙስሊም ወንድም ነው፡፡ አይበድለውም አያቃልለውም አይንቀውም አላህን ፍራቻ እዚህ ውስጥ ነው፡፡) ሦስት ጊዜ ቃሉን ሲደጋግሙ ወደልባቸው አያመለከቱ ነበር፡፡ (አንድ ሰው ወንወጀል ለመፈጸም ሙስሊም ወንድሙን ማንኳሰሱ ይበቀዋል፡፡ የአንደን ሙስሊም ደም፣ንብረትና ክብር በማንኛውም ሙስሊም ላይ የተከለከለ ነው፡፡ )መልካም ሥራ መን ማለት እንደሆነ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ሲያብራሩ አንድህ ይላሉ፡ (አላህን ስትገዛ ልክ ከፊት እንዳለ አድረገህ መሆን አለበት፡፡ አንተ ባታየውም እሱ ያሃልና፡፡) በዚህም አንድ ባሪያ ጌታው በምስጢርም ሆነ በይፋ አየተንቀሳቀሰም ይሁን ጽጥ ብሎ የሚሰራውን ነገር ሙሉ በሙሉ የሚቆጣተረው መሆኑን በግልጽ የተገነዘበ ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ‹አላህ የሚያይ መሆኑን አላወቀምን› ይላል፡፡
አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር እንዲሆን ከሚያደርጉ ነገሮች ሌላው ትእግስት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ታገስ አላህ ከነዚያ ከታጋሾቹ ጋር ነውና ይላል፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَبَشِّرِالصَّابِرِينَ * الَّذِينَ إِذَاأَصَابَتْهُمْ مُصِيبَةٌ قَالُواإِنَّالِلَّهِ وَإِنَّاإِلَيْهِ رَاجِعُونَ * أُولَئِكَ عَلَيْهِمْ صَلَوَاتٌ مِنْ رَبِّهِمْ وَرَحْمَةٌ وَأُولَئِكَ هُمُ الْمُهْتَدُونَ}**

ትርጉሙም (ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡ እነዚያን መከራ፤ በነካቻቸው ጊዜ «እኛ ለአላህ፤ ነን እኛም ወደርሱ ተመላሾች» ነን የሚሉትን (አብስር) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (እወቅ በምትጠላው ነገር በመታገሰው በዙ ደግ ነገር አለ) ትእግስት ማለት ስቃይ በሚደርስ ጊዜ መፍስን ሮሮ እንዳታሰማ፣ ምላስን አቤቱታ እንዳያበዛ፣ ሌሎችንም አካላት ከመርበርበት መግታት ነው፡፡ እሱም መንፈስን መዋጋት ግድ ይላል፡፡ ነብያችን ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለትግስት የተዘጋጀን ሰው ትእግስት ይሰጠዋል፡ አንድ ሰው ከተሰተው ነገር ሁሉ ከትእግት የሰፋ ነገር አልተሰጠም፡፡)

አላህ (ዐ.ወ.) ከባሪያወ  ጋር እንዲሆን የሚያደርገው ሌላው ነገር ደግሞ የአእምሮ ንቃት ነው፡፡ አንድ ሰው አላህ (ዐ.ወ.) በመንገድም ሆነ በአገር ቤት፣ ቤት ውስጥም ይሁን በአደባባይ የሚሰራውን ስራ በእውቀቱ ያከተተው መሆኑን ሲገነዘብ አይምሮ ንቁ ይባላል፡፡ ይህን ጉዳይ ሰይዲና ዩሱፍ (በአላህ እጠበቃለሁ እርሱ (የገዛኝ) ጌታዬ ኑሮዬን ያሳመረልኝ ነውና፤ (አልከዳውም)፡፡ እነሆ! በደለኞች አይድኑም») በማለታቸው ግልጽ አድርገውታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በቁድስ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (በአሸናፊነቴ ይሁንብኝ እኔ በባሪያዬ ላይ ሁለት ፈርሃትን እንድሁም ሀለት አለመፍራትን በአንድ ላይ አልፈርድበትም፡፡ በዚህች አለም እኔ የማይፈራ ከሆነ በትንሳኤ ቀን እንድፈራ አደርገዋለሁ፡፡ በዚህች ዓለም የሚፈራኝ ከሆነ ደግሞ በትንሳኤ ቀን ፍርሃት እንዳያገኘው አደርጋለሁ፡፡)
አንድ ሰው አላህን አብዝቶ በማውሳቱም አላህ ከሱ ጋር ይሆናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡ (አስታውሱኝ አስታውሳችኋለሁ፡፡ ለኔ አመስግኑ አትካዱኝም፡፡) ነብኛችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡ እኔ ባሪያዬ እንደሚያስበኝ ከሱ ጋር ያገኘኛል ለብቻው ካሰበኝ እንደዚሁ አስበዋለሁ፡፡ ከሰዎችም ጋር ካስታወሰኝ ከነሱ በበለጡ በሪያወች ፊት አስታውሰዋለሁ፡፡)

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

አንድ ሰው አላህ ከሱ ጋር በመሆኑ በዚህች ዓለምም ሆነ በመጨው ዓለም የሚያገኘው ታላቅ መልካም ውጤት አለው፡፡ አላህ ከሱ ጋር የሆነ ሰው እሱ ከማንኛውም ተንኮል ይጠብቀዋል፡፡ ጎጂ ነገር ሁሉ ከሱ ገለል ያደርግለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{الَّذِين َقَالَ لَهُمُ النَّاسُ إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُم ْإِيمَانًا وَقَالُواحَسْبُنَااللَّهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ}**

ትርጉሙም(እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- «ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው» ይሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ!» ያሉ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{وَمَنْ يَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ فَهُوَحَسْبُهُ إِنَّاللَّهَ بَالِغُ أَمْرِهِ قَدْجَعَلَ اللَّه كُلِّ شَيْءٍ قَدْرًا}**

ትርጉሙም (በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፡፡ አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል፡፡) ማት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡ (አላህ ባሪያውን በቂ አይደለምን?)

በአላህ የተመካና እሱ እንደሚያግዘው እርግጠኛ የሆነ ሰው ጠላት አይደፍረውም፣ ቢጠይቅ አያሳፍረውም፣ የፈለገውንም አያሳጣው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለነብዩ ሙሳ «ለነፍሴም (በመልእክቴ) መረጥኩህ፡፡» እንድሁም ‹‹በእኔም ጥበቃ ታድግ ዘንድ፡፡›› ለነብያችን (ሶ.ወ.) ደግሞ ‹‹ለጌታህ ፍርድም ታገሥ፡፡ አንተ በጥበቃችን ውስጥ ነህና፡፡›› እንድሁም ‹‹ለእነሱ ከጌታቸው ዘንድ መልካም ምንዳ ያላቸው መኾኑን አብስር» ማለቱን ስንመራመር የአላህ ከኛ ጋር መሆንን ታላቅነትና መልካም ውጤቱን በግልጽ አእንገነዘባለን፡፡

ወደአላህ አብሮነት መግባት በሱም በዘላቂነት መቆየት የእርጋታና የመንፈስ እርካታ እንድሁም ከጭንቀትና መረበሽ የመራቅ መሰረት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ምክኒያቱም ትክከለኛውን መሰረት የጣለና ማንኛውም ነገር በአላህ እጅ መሆኑን ያረጋገጠ ሰው ለምን ይጨነቃል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{قُلِ اللَّهُمَّ مَالِكَ الْمُلْكِ تُؤْتِي الْمُلْكَ مَنْ تَشَاءُ وَتَنْزِعُ الْمُلْكَ مِمَّنْ تَشَاءُ وَتُعِزُّ مَنْ تَشَاءُ وَتُذِلُّ مَنْ تَشَاءُ بِيَدِكَ الْخَيْرُ إِنَّكَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ}

ትርጉሙም ((ሙሐመድ ሆይ!) በል፡- «የንግስና ባለቤት የኾንክ አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግሥናን ትሰጣለህ፡፡ ከምትሻውም ሰው ንግሥናን ትገፍፋለህ፡፡ የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ፡፡ የምትሻውንም ሰው ታዋርዳለህ፡፡ መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና፡፡» ማለት ነው፡፡ እንድሁም እንድህ ይላል፡

{ما يَفْتَح اللَّهُ لِلنَّاسِ مِن رَّحْمَةٍ فَلَا مُمْسِكَ لَهَا وَمَايُمْسِكْ فَلَامُرْسِلَ لَهُ مِن بَعْدِهِ وَهُوَالْعَزِيزُ الْحَكِيمُ}.

ትርጉሙም (አላህ ለሰዎች ከችሮታ የሚከፍታት ለእርሷ ምንም አጋጅ የላትም፡፡ የሚያግደውም ከእርሱ በኋላ ለእርሱ ምንም ለቃቂ የለውም፡፡ እርሱም አሸነፊው ጥበበኛው ነው፡፡) ማት ነው፡፡

የአላህ ባሮች አላህ ከነሱ ጋር መሆኑን ሲያስቡ የእሱን ማሰብ ታላቅነት ሲገመግሙ ለነሱ የመንፈስ እርካታ የመልካም አብሮ መኖርና የማህበረሰብ ደህንነት መረጋገጡን ይገነዘባሉ፡፡ የአላህ ባሮች በማንኛውም ጊዜና ቦታ አላህ ከነሱ የማይርቅ መሆኑን ሲያረጋግጡ ስርኣተ ጥሩና ጠባየ መልካም ይሆናሉ፡፡ የአላህን ትእዛዝ ይፈፈጽማሉ የከለከለውንም ሁሉ አጥብቀው ይርቃሉ፡፡ የዚህችን ዓለምና የመጭውን ዓለም ጉዳዮች ለማሻሻልም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ያ ግለሰቡም ከቤተሰቡ፣ ከማህበረሰቡ፣ ከጓደኞቹ ጋር በሰላምና በጸጥታ ይኖራል፡፡ ይህም ለሰዎች እዝነት የመጣው የእስልምና ሃይማኖት ዋና መልእክት ነው፡፡

ጌታችን ሆይ! የእርዳታህ አብሮነት አይለየን፡፡ በሰፊው ችሮታህም የተካተትን አድርገን፡፡ ጸጋዎችህንም አስፋልን፡፡ በነገራችን ሁሉ ታማኝነተን ለግሰን፡፡ ሀገራችንም ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡